የሰ/መ/ቁ. 73569

ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- አቶ ደረጀ ጎሳዬ - ጠበቃ ወገኔ ካሳሁን ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አቃቤ ሕግ የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለዋስትና የተያዘ ገንዘብ ይመለስልኝ ጥየቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል በሶስት ምድብ የተከፈለ ክስ ቀርቦበት ፍርድ ቤቱ ለአመልካች የዋስትና መብቱን ጠብቆለት አመልካች ብር 500,000.00(አምስት መቶ ሺህ ብር) አስይዞ የተጠበቀለትን የዋስትና መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ ሲፈልግ በቼክ ጉዳይ በወንጀል ተከሶ የእስር ቅጣት በመፈረዱ ምክንያት ማረሚያ ቤት በመግባቱ የዋስትና መብቱን ሊጠቀምበት ያለመቻሉን ገልጾ በክርክር ሂደት ላይ ላለው ጉዳይ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲመለስለትና ጉዳዩን ከማረሚያ ቤት እየተመላለሰ እንዲከታተል ይደረግ ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታው በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 75 መሠረት ይግባኙ የቀረበበት መሆኑን ገልፆና ይህ ድንጋጌ የሚያገለግለው የዋስትና መብት ሲነፈግ ይግባኝ ለማቅረብ ነው የሚል ምክንያት ይዞ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም አመልካች በሌላ ወንጀል በተፈረደው ፍርድ መሠረት ማረሚያ ቤት የሚቆይ በመሆኑ ለሌላ ጉዳይ የተጠበቀው የዋስትና መብት ተግባራዊ የማይሆን መሆኑ ግልጽ ስለሆነ ለጉዳዩ የተያዘው ገንዘብ እንዲመለስ መጠየቁ ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በሌላ መዝገብ ፍርደኛ በመሆኑ ከማረሚያ ቤት ተመላልሶ መከራከር የሚችል ቢሆንም ለዋስትና ያስያዘው ገንዘብ አይመለስለትም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ተጠሪ ቀርቦ በጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር

በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡
አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የዋስትና ገንዘብ ያስያዘው በተጠሪ መስሪያ ቤት አቃቤ ሕግ የተለያዩ የጉምሩክ ሕግ ድንጋጌዎች ተላልፏል ተብሎ በቀረቡት ሶስት ክሶች የዋስትና መብት በፍርድ ሲጠበቅለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በቼክ ጉዳይ ተከሶ የአራት አመት ከስድስት ወር ፍርደኛ ሆኗል፡፡ ገንዘቡ እንዲመለስለት የሚጠይቀውም ፍርድ ቤት ያለውን የጉምሩክ ወንጀል ክርክርን ከማረሚያ ቤት በመመላለስ የሚከታተል መሆኑን በመገንዘብ ነው፡፡

በመሰረቱ ዋስትና ሕገ መንግሥታዊ መብት መሆኑንና ይህ መብት በልዩ ሁኔታ በሕጉ ክልከላ ካልተደረገ በስተቀር ለተከሰሱ ሰዎች ሊጠበቅ የሚችል መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 19(6) ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ በሕጉ አግባብ የዋስትና መብት ሲፈቀድ ደግሞ የተከሳሹ ፍርድ ቤት መቅረብ እውን እንዲሆን ተከሳሹ ገንዘብ እንዲያስይዝ ወይም ሌላ ዋስትና እንዲያቀርብ የሚደረግ መሆኑን የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 69(1) ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ የዋስትና መብት የተፈቀደለት ተከሳሽ መብቱን ለመቀጠም የማያስችል ሕጋዊ ምክንያት ያለው መሆኑን በመግለፅ መብቱን ለመጠቀም ካልፈለገ ደግሞ መብቱ የራሱ ይሆናል፡፡ በፍርድ ቤት የተፈቀደለትን የዋስትና መብት ያለመጠቀም ፍላጎት ደግሞ የዋስትና መብት እንደተፈቀደ ወይም ከተፈቀደና ተከሳሹ መብቱን መጠቀም ከጀመረ በኂላም ሊመጣ ይችላል፡፡ ሕጋዊ ምክንያት እስካለው ድረስ በማንኛውም ደረጃ ተከሳሹ በሕጉ አግባብ የተፈቀደለትን የዋስትና መብት የመተው ፍላጎቱ ሊጠበቅለት የሚገባው ጉዳይ እንጂ ይህንኑ መብቱን ለመከላከል የሚያስችል ግልጽ ድንጋጌ የለም፡፡ ፍርድ ቤቱ ትኩረት ሊያደርግና ሊቆጣጠረው የሚገባው ቁልፍና ዋናው ነገር በፍርድ ቤት ክስ የቀረበበት ሰው ቀጠሮውን ተከታትሎ የሚቀርብበት ትዕዛዝ መስጠቱ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የተከሳሽን የዋስትና መብት በማክበር ተገቢውን ዋስትና በማስጠራት ወይም ተከሳሹ ማረሚያ ቤት ሆኖ ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 68 እና 69 ድንንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ተከሳሽ የዋስትና መብቱ ከተከበረለት በኂላ በሕጋዊ ምክንያቶች መብቱን በመተው ጉዳዩን ማረሚያ ቤት ሆኖ ለመከታተል ፍላጎት ያለው መሆኑን ሲገለጽ ሊነፈግ አይገባም፡፡ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄ ያልተቀበለው አመልካች በዋስ የተለቀቀበት መዝገብ እልባት ያላገኘና ማረሚያ ቤት በሌላ ወንጀል ገብቷል የተባለውም በውሳኔ ይሁን በሌላ ምክንያት አልተረጋገጠም በሚል ሲሆን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ይግባኙ የሚቀርበው የዋስትና መብት ሲከለከል ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በሌላ ወንጀል ፍርደኛ መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 75"ን" ለአቤቱታው መሠረት ማድረጉም አቤቱታውን ለማስተናገድ ፍርድ ቤቱ አልችልም ብሎ ውድቅ ለማድረግ ሥነ ሥርዓታዊ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ፍርድ ቤቶቹ አመልካች እልባት ያላገኘውን ጉዳይ ከማረሚያ ቤት በመመላለስ የፍርድ ቤትን ቀነ ቀጠሮውን አክብሮ የሚከታተልበት አግባብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ትዕዛዝ በመስጠት ይህንኑም እንዲፈፅም ለማረሚያ ቤቱ ማስተላለፍ ሲገባቸው ሕጋዊ መሠረት የሌላቸውን ምክንያቶችን በመያዝ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ከአመልካች የንብረት መብትና መብቱ ሊያስገኝ የሚችለውን ፍሬ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 68 እና 69 ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 174010 የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 106592 ሐምሌ 08 ቀን 2003 ዓ/ም የጸናው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 174010 በቀረቡት ክሶች ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲመለስለት ብለናል፡፡ አመልካች በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጉዳይ ማረሚያ ቤት ሆኖ እንዲከታተል የማሰሪያ ዋራንት ለማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ለአመልካች ገንዘቡን እንዲያስመልስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ሀ